ይህን መጽሐፍ ቅዱስ በቅናሽ ዋጋ እንዲቀርብ የረዱት በዓለም አቀፍ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስን በማሰራጨት አገልግሎት የተሰማሩት ‹‹ፎረም ኦፍ ባይብል ኤጀንሲስ›› (FORUM OF BIBLE AGENCIES) በመባል የታወቁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ድርጅቶችና ሌሎችም ናቸው።

| | |
|---|---|
| 1. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበሮች | United Bible Societies |
| 2. ኢንተርናሽናል ባይብል ሦሳይቲ | International Bible Society |
| 3. ዘባይብል ሊግ | The Bible League |
| 4. ኦፐን ዶርስ | Open Doors |
| 5. ባይብል ፎር ዘወርልድ | Bible for the World |
| 6. ባይብል ሊትሬቸር ኢንተርናሽናል | Bible Literature International |
| 7. ባይብልስ ቱ ኦል | Bibles to All |
| 8. ስክሪፕቸር ጊፍት ሚሽን | Scripture Gift Mission |
| 9. የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ማኅበር | Scripture Union |

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያናት በረከት ለምዕመናንም መንፈሳዊ እድገትና መጽናናት እንዲሆን የአቅራቢዎቹ ምኞትና ጸሎት ነው።

# መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ።

## የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፤


የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

መጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ (DC R043) በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታተመ ።

፲፱፻፹ ዓ.ም.

United Bible Societies
Africa Regional Centre
P.O.Box 42726
Nairobi, Kenya

Amharic Bible
UBS–EPF 1992–50M–DCR043

ISBN 9966 40 407 4

# መቅድም ።

ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምራ እንደ ጊዜው ሁኔታና እንደ ሕዝቡ አኗኗር ሁሉም በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም ትምህርትና ዕውቀት እንዲያድግ ሕዝቡን ስታስተምርና ስትረዳ ኖራለች ።

አሁንም መሠረታዊ ዓላማዋን ጠብቃ ይህንኑ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትዋን ለጊዜው ትውልድ በሚበጅና በሚጠቅም ሁኔታ እያደራጀች መቀጠል ያለበት መሆኑን በመገንዘብ የማሳተሚያ ድርጅት አቋቁማ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ አስፈላጊነታቸው በግእዝና በአማርኛ እያሳተመች መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮዋን በተሟላ ሁኔታ በመፈጸም ላይ ትገኛለች ።

እንዲሁም ቅዱስ ሲኖዶሳችን ቀደም ሲል ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጕመውና ታትመው የነበሩትና አሁን ለአገልግሎት ሲፈለጉ የማይገኙት እንደገና እየታተሙ እንዲቀርቡ ከዚህ በፊት ያልታተሙትም በጊዜው ያለውንና የሚቀጥለውን ትውልድ ለማገልገል በሚችሉበት ሁኔታ የአማርኛ ትርጕማቸው ከዘራቸው (ከንባባቸው) ሳይፋለስ በጥንቃቄ እየተዘጋጁ እንዲታተሙ በማድረግና ሥነ ጽሑፍን በማስፋፋት ላይ ነው ።

በዚህም መሠረት በውስጡ ፵፮ የብሉይ ኪዳን ፤ ፳፯ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የያዘውና በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ታትሞ የነበረው ትልቁ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ የታተመው ተሰራጭቶ በማለቁ እንደገና አሳትሞ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ስለተገነዘብን በውስጡ ከቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት አባባል ውጭ የሆኑትንና ከግእዙ ጋር የማይስማሙትን ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ቅዱስ ሲኖዶሳችን ከተመለከታቸውና ከአስተካከላቸው በ ላ እንደገና እንዲታተም አደረግን ።

ከግእዙና ከአማርኛው ምንባብ ጋር የማይገናዘቡና ከምርመራ ያመለጡ ባዕዳን ቃላት ቢገኙ የመጽሐፍ ኅትመት በአንድ ጊዜ ፍጹም ሊሆን ስለማይችል ከአንባብያን የሚቀርቡልንን ሰብስበን እንደገና በሚታተምበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ ታርሞና ተስተካክሎ ሊታተም ይችላል ።

ከቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት አነጋገርና ከግእዙ ጋር እንዲስማሙ.የተደረጉት ቃላትና ዓርፍተ ነገሮች አልፎ አልፎ ብሉይ ኪዳንን በሚመለከት ከዕብራይስጡ ፤ ሐዲስ ኪዳንን በሚመለከት ከግሪኩ የተለዩትን ፤ በዕብራይስጡና በግሪኩ እንደ፦ት እንደሚል በኅዳጉ (በፉትኖት መልክ) እንዲታይ ተደርጎአል ።

«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ፤ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» እንደሚለው ሁሉ ከመጻሕፍት የሚገኘው ብርሃን ለሁሉ እንዲያበራ ማድረግ የቤተ ክርስቲያናችን ተቀዳሚ ተግባር ስለሆነ ፤ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በሲኖዶስ አባላት ተመርምሮና ሊስተካከል የሚገባው ተስተካክሎ በዘመነ ፓትርያርክነታችን በአሥራ አንደኛው ዓመት ታተመ ። የማሳተሚያ ገንዘብ የረዳንን የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፤ በኅትመቱ ሥራ የተራዱንና ያገለገሉንን ሁሉ ከልብ እናመሰግናቸዋለን ።

አባ ተክለ ሃይማኖት

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

